*ለተማሪዎች መመሪያ*

# *የጾታ ማንነት*

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

የሥራ ባልደረቦች እና ተማሪዎች በሙሉ የጾታ ምንነት/ማንነት-መለያ ጉዳዮችን በተመለከተ ልውጥ ጾታን እና ጾታቸው በውል ያልተገለጸ ተማሪዎችን እውቅና መስጠት እና ማክበር አስፈላጊ ሲሆን እንደዚህ አይነት ተማሪዎች ጾታቸውን ለመግለጽ እንዲችሉ ምቾት እንዲሰማቸው ያስፈልጋል። ለተግባራዊነቱ እስከ ተቻለ መጠን፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጾታ ማንነት ጥያቄዎችን እና የተማሪ ግላዊ ገመናን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ/ለማስተናገድ ይጥራል። ተማሪዎች በትምህርት እንዲጠመዱ እና በት /ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት እና ዋጋ እንዳላቸው ተሰምቷቸዉ ንቁ ተሳታፊዎች የሚሆኑበት ደህንነቱ የተጠበቀ/ ሰላማዊ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲኖር የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቁርጠኝነት አለው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ዋና እሴቶች መሠረት፣ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ መመሪያ ጋር የተጣጣሙ የሚከተሉት መመሪያዎች እና የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል አድሎአዊነት፣ በሰው ላይ መጠቋቆም/ማግለል፣ እና ጥቃት-ጭቆና በቸልታ እንደማይታለፍ በዲስትሪክት አቀፍ የተጠበቀ መሆኑ ተቀምጧል። በዚህ መመሪያ ሊሆን የሚችል እያንዳንዱን ክስተት ሁሉ ለመተንበይ አይቻልም። ከዚህም የተነሣ፣ የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎቶች በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በመመስረት ግምገማ ሊደረግበት ይገባል።

## ግቦች

- ተማሪዎች ከጾታዊ ማንነታቸዉ ጋር ከሚጣጣም በትምህርት ቤት ህይወት ለመሳተፍ እንዲችሉ መርዳት፤
- የጾታ መገለጫቸውን እንዲጠብቁና እና ጾታ የቀየሩት የግል አቋማቸው በሚስጥር እንዲያዝ የተማሪዎችን መብት ማክበር፣
- ጾታቸውን በቀየሩት ላይ እና ሥርዓተ-ፆታን በማያሟሉ ተማሪዎች ላይ የሚደረግ የማግለል/የመጠቋቆም፣ እና ዝቅ አድርጎ የማየትን ሁኔታ መቀነስ፤
- ጾታቸውን የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን የማያሟሉ ተማሪዎችን ማህበራዊ ዉህደት እና በአብሮነት የማቀፍ ባህልን ማሳደግ/ማበረታታት፤ እና
- ለ MCPS የሥራ ባልደረቦች የተማሪ ጾታ ምንነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን በአግባብ እና በቀጣይነት እንዲተገበሩ የሚያስችል ድጋፍ መስጠት።

## ትርጉም

እዚህ ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች ልውጥ ጾታ እና ጾታቸውን መግለጽ ያልቻሉ ተማሪዎችን ለመደገፍ እንጂ ተማሪዎችን ለመፈረጅ ታስቦ አይደለም። ተማሪዎች እራሳቸውን ለመግለጽ እነዚህን ቃሎች ሊጠቀሙ ወይም ላይጠቀሙ ይችላሉ።[3፣4]

**ጾታ የለሽ/AGENDER ጾታ** አልባ ("ጾታ አልባነት/nongendered" ወይም "ጾታ የለሽነት/genderless")።

**የተወለደ(ች)በት ጾታ ስያሜ/CISGENDER** የጾታ ማንነት እና የጾታ አገላለጽ የተወለደ(ች)በትን የጾታ ስያሜ የያዘ/ች ሰው፣ ጾታ ያልቀየረ/ች ሰው ወይም ሥርዓተ-ፆታ የማያሟላ/የማታሟላ(የማያረጋግጥ/የማታረጋግጥ) ሰው።

**የጾታ አገላለጽ ሰው አብዛኛውን ጊዜ በባህርይ፣** በአለባበስ፣ በፀጉር አሠራር፣ በእንቅስቃሴዎች፣ በድምፅ፣ በንግግር እና የቃላት አመራረጥ፣ ወይም ለየት ያለ የአነጋገር ዘዬ የራሱን/የራሷን ጾታ ለሌሎች የሚገልጽበት/የምትገልጽበት ባህርይ ነው።

**የሥርዓተ-ፆታ መዋለል (ወላዋይ ፆታዊ ይዘት)/GENDER FLUID** የጾታ ማንነቱ(ቷ) ወይም የጾታ መገለጫዉ/ዋ ቋሚ ያልሆነ እና እንደ ሁኔታው በጊዜ ሂደት የሚለዋወጥ።

**የጾታ ማንነት የአንድ/የአንዲት ሰው/ሴት ስለ ስለራሱ(ሷ) ጾታ በጥልቀት የያዘ(ች)ው የተገነዘበ(ች)ው ስነልቦናዊ እውቀት።** የአንድ ሰው የጾታ መገለጫ በትውልድ ከተሰጠው/ከተሰጣት የጾታ ማንነት ጋር አንድ ዓይነት ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች በተወለዱ ጊዜ ከተሰየሙት የጾታ መለያ/ማንነት ጋር የሚገጣጠም የጾታ መገለጫ አላቸው። ቢሆንም እንኳ፣ ለአንዳንዶች፣ የፆታ ማንነታቸው በተወለዱበት ጊዜ ከተሰየመላቸው የፆታ መለያ የተለየ ነው። ጾታቸውን የቀየሩ ወይም ጾታቸውን የማያረጋግጡ/የማይገልጹ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰዎች ሁሉ የጾታ ማንነት አላቸው። ለዚህ መመሪያ ዓላማ፣ የአንድ ተማሪ ፆታው(ዋ) በት/ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ በይፋ የታወቀ/የተረጋገጠው ነው።

**GENDER NONCONFORMING/ሥርዓተ -ፆታ የማያሟሉ** በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ካለው/ከተለመደው/ባህላዊ ከሆነው የተለየ አገላለጽ ወይም የተወሰነ ወይም "አነስታይ/feminine" ወንዶች፣ "ተባታይ/masculine" ልጃገረዶች፣ የማይለወጥ አመለካከት የመሣሠሉ እና ጾታዊ አገላለጻቸው አንድሮጅነስ/androgynous/ከፊል ወንድ ከፊል ሴት የሆነ/ች። ይህ የሚያካትተው በተለምዶ ከሚታወቀው ዓይነት የፆታ አገላለጽ ስያሜ ውጪ ወይም እንደ ሁለት ወይም የበለጠ (የተለየ) ፆታዊ ማንነት እንዳላቸው የሚገልፁትን ነው። ሌሎች ተመሳሳይ ትርጓሜዎች ሊኖራቸው የሚችሉ ቃላት የሚያካትቱት "የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት/ልዩ ልዩ ፆታ" ወይም "ጾታን የሚያራምዱ/የሚያስፋፉ" ናቸው።

**በምህጻረ ቃሉ LGBTQ ማለት ከመሰል ጾታ ጋር ወሲብ የምትፈጽም ሴት፣** ጌይ/ወንድ ከወንድ ጋር ሩካቤ ስጋ ፈጻሚ፣ Bisexual/ለሁለቱም ጾታ ለሩካቤ ስጋ የሚ(ምት)ሳብ፣ ጾታ የቀየረ/ች፣ Queer/የጾታ ልዩነቶችን የማይ(ት)ቀበል/ እና ማህበረሰብን የሚጠይቁ። ይህ ምህፃረ ቃል ብዙውን ጊዜ ሁሉን ያካተተ ለማድረግ ሲባል LGBTQ + ተብሎ ይጻፋል።

**በመወለጃ ጊዜ የተሰየመ ጾታ በህፃንነት የልደት ሠርተፊኬት ላይ የተሰየመ ጾታ፣** በልደት ቀን/በተወለዱበት ቀን እንዲህ ዓይነት ሰነድ/ምዝገባ መሰጠት አለበት።

**የጾታ ለውጥ የአንድ ሰው የጾታ ማንነት ወይም መገለጫ ከተለመደው በተወለደ/ች ጊዜ ከተሰየመ ጾታ የተለየ ቅጽላዊ አገላለጽ ነው።** ተመሣሣይ ትርጉም የሚኖራቸው ሌሎች ቃሎች " ቅይር ሴት/ወንድ transsexual (ሴት ነኝ ብሎ የሚያምን ወንድ/ወንድ ነኝ ብላ የምታምን ሴት-- በቀዶ ጥገና ፆታውን ያስቀየረ/ያስቀየረች) " እና " ቅይር/trans "

**ሽግግር** ማለት አንድ ሰው በተወለደ(ች)በት ወቅት ከተሰየመ የጾታ ምንነት ይልቅ ራሱ(ሷ)ን ነኝ ብሎ(ላ) ባመነ(ች)በት ጾታ ለመኖር የመወሰን ሂደት ነው። ጾታቸውን የቀየሩ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ስለራሳቸው ጾታ ማንነት ለመግለጽ የተለያዩ አይነት ዘይቤዎችን/እርምጃዎችን ይጠቀሙ ይሆናል (ለምሣሌ:- ስመሞክሼነትን/ተቀጽላ ስም መጠቀም፣ ወይም በህጋዊ ሠነዶቻቸው ላይ እና/ወይም የጾታ ስያሜአቸውን ማስቀየር፣ ጾታቸውን ገላጭ የሆነ አለባበስ እና የፀጉር አሠራር፣ እና በአጠቃላይ በቋሚነት የእነርሱን ጾታ ማንነት ለሎች በማንፀባረቅ መኖር)። ጥቂቶች፣ ነገር ግን ሁሉም አይሆኑም፣ ፆታቸውን የሚቀይሩ ሰዎች እድገ-ንጥር/ሆርሞን/ መድኃኒት ይወስዳሉ ወይም በቀዶ ጥገና ህክምና ተለውጦ ሰውነታቸው ከፆታ ማንነታቸው ጋር እንዲመሣሰል ያስደርጋሉ። በሽግግር የአንድን ሰው የጾታ ማንነት ማህበረሰባዊ አገላለጽን የሚያካትት ቢሆንም ሽግግር ግላዊ የሆነ ሂደት ስለሆነ ግለሰቦች የግል ገመና መብት አላቸው።

---

ተዛማጅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን እና የ MCPS ደንቦች/Related Montgomery County Board of Education Policies and MCPS Regulations፡- ACA, ACF, JHF, JHF-RA, ACA-RA, ACF-RA

[2]የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት እና የተጨማሪ መገልገያዎችን ዝርዝር ለማወቅ ይመልከቱ፡- የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ጾታ የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን ላላሟሉ ወጣቶች ሰላማዊ/የማያሰጋ ስፍራ መስጠት፡- በጾታ ማንነት ምክንያት አድሎ እንደማይደረግ መመሪያ(አክቶበር 2015)፣ በ ይገኛል፤ marylandpublicschools.org/about/Documents/DSFSS/SSSP/ProvidingSafeSpacesTransgendergenderNonConformingYouth012016.pdf።

[3]በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጸው ሃረግ በተቻለ መጠን ሁሉን ያካተተ እንዲሆን የታሰበ ነው፣ ቢሆንም ግን፣ ሃረጎቹ እና ቋንቋ ቀስበቀስ የሚያድግ እና ቶሎ ወቅት የሚያልፍበት/የሚያረጅ እንደሆነ ግልጽ ነው።

[4]ፍቺ/ትርጉሞቹ የተሰጡት ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ምንጮች ነው፡- American Civil Liberties Union; American Psychological Association; California School Boards Association; Chicago Public Schools; District of Columbia Public Schools; Gay, Lesbian, and Straight Education Network; Howard County Public Schools; Human Rights Campaign; Lambda Legal; Maryland State Department of Education; Maryland Public Secondary Schools Athletic Association; Massachusetts Department of Elementary and Secondary Education; National Collegiate Athletic Association; National School Boards Association; New York City Department of Education; and Trevor Project.

## ፆታ ከቀየሩ እና ፆታቸውን ከማይገልጹ ተማሪዎች ጋር በቀዳሚነት/PROACTIVELY አብሮ መሥራት

- ርእሰመምህር (ተወካይ)፣ ከተማሪዎች እና ከወላጆቻቸው ጋር ቤተሰብ ጋር በመተባበር (ቤተሰቡ ተማሪው(ዋ)ን የሚደግፉ ከሆነ)፣ በት/ቤት ጠቅላላ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ በእኩል የመሣተፍ እድል እንዲኖራቸው እና በት/ቤት ጾታን መሠረት -ያደረገ አድሎአዊነት ለመከላከል የሚያስችል እቅድ/ፕላን ማዘጋጀት አለባቸው። ርእሰ መምህር፣ ተወካይ፣ ወይም ት/ቤትን መሠረት ያደረገ የአእምሮ ጤና ባለሙያ (ለምሳሌ:- የት/ቤት ስነልቦና ባለሙያ ወይም የት/ቤት ካውንስለር) MCPS Form 560-80 ቅጽ መጠቀም አለባቸው:- የመቀበያ ቅጽ:- ተማሪዎችን መደገፍ፣ የጾታ ማንነት(አባሪ/Attachment A-1) በት/ቤት ተሳትፎ ተማሪን ለመደገፍ ይህንን ሂደት ለመደገፍ። የተሞላው ቅጽ በተማሪ ፋይል ማጠራቀሚያ ወይም ሚስጥራዊ ፋይሎች ላይ ሳይሆን አስተማማኝ በሆነ ስፍራ መቀመጥ አለበት። እቅዱ/ፕላኑ በሁሉም የት/ቤት ባልደረቦች በትክክል/በቋሚነት የሚተገበር ቢሆንም ቅጹ ራሱ በሌሎች የት/ቤት ባልደረቦች መታየት ወይም ሊጠቀሙበት አይገባም።
- የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት እንደ ጉዳዩ ሁኔታ አንድ-በአንድ መገምገም አለበት፣ እና ሁሉም እቅድ በሂደት እየተገመገመ እንደአስፈላጊነቱ ይከለሳል። ት/ቤቶች አንድ ቁልፍ የሆነ/ች ተማሪዎች የሚገናኙ/ኟት ሰው(ሰዎች) የእቅዳቸው አካል አድርገው መመደብ/መለየት አለባቸው። እንዴት ድጋፍ እንደሚሰጥ፣ እንዴትና ለማን ኢንፎርሜሽን መነገር እንዳለበት በእቅዱ ላይ መገለጽ/መታየት/መነደፍ አለበት። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ ፕላን/እቅድ ተፈላጊውን ስም፣ ተውላጠ ስም፣ አትሌቲክስ፣ ከከሪኩለም ተጨማሪ እንቅስቃሴዎችን፣ የሎከር ክፍሎችን፣ የመፀዳጃ ክፍሎችን፣ ሠላማዊ ስፍራዎችን፣ ሠላማዊ አካባቢዎችን፣ እና ሌሎችም የደህንነት/ሠላማዊ ድጋፎችን፣ እና ምረቃን የመሣሠሉ ገሃዳዊ ሁነቶችን ማካተት አለበት።
- ርእሰ መምህሩ/ሯ ወይም የተመደበው/ችዉ ግለሰብ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር ከመነጋገራቸው አስቀድመው፣ ከቤት ምን ያህል ድጋፍ እንዳለው/እንዳላት ወይም ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚጠብቅ/እንደምትጠብቅ ለማረጋገጥ ከተማሪው(ዋ) ጋር መነጋገር አለባቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን ይፋ የማያደርጉ ተማሪዎች ስለደህንነታቸው በመስጋት ወይም ተቀባይነት ስለማይኖር ቤት ውስጥ በገሃድ ስለጾታቸው አይናገሩም ይሆናል። የጾታ ማንነት ጉዳዮች ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ እና ቤተሰባዊ ግጭትም ሊያስከትል ይችላል፣ ጉዳዩ እንደዚህ ከሆነና ድጋፍ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ለት/ቤት ድጋፍ እና መሻሻል ጽ/ቤት ወይም የተማሪ እና ለቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት (OSFSE) መግለጽ አስፈላጊ ነው።

## መረጃ/ኢንፎርሜሽን ይፋ ማድረግ እና ግላዊነት

- ሁሉም ተማሪዎች ስለግል ገመናቸው መብት አላቸው። ይህ የሚያካትተው የጾታ ለውጥ ያደረጉ ወይም ጾታ የማይገልጹትን ግላዊ አቋም በት/ቤት ገመና የመጠበቅ መብት ነው።
- ስለ አንድ ተማሪ የፆታ መቀየር አቋም፣ ህጋዊ ስም፣ ወይም በተወለደ(ች) ጊዜ የተሰጠ ፆታ ከህክምና ጋር የሚገናኝ ሚስጥራዊ መረጃ ሊሆን ይችላል። ይህን ዓይነት መረጃ ለሌሎች ተማሪዎች መግለጥ፣ ወይም ለወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው፣ ወይም ለሦስተኛ ወገን ማጋለጥ የግል ገመናን ህግ እንደ ፌደራል "የቤተሰብ የትምህርት መብት እና የግል ገመና ደንብ" (FERPA) መጣስ ይሆናል።
- ሁሉም የህክምና መረጃዎች/ኢንፎርሜሽን፣ ከጾታ መቀየር ጋር የሚዛመዱትን ጭምር፣ የስቴት፣ አካባቢ፣ እና በፌደራል የግል ገመና አጠባበቅ ህጎች ድንጋጌዎች መሠረት በሚስጥር እንደተጠበቁ ት/ቤቶች ማረጋገጥ አለባቸው።
- ስለ ጾታ አቀራረብ፣ ማንነት፣ እና ብዙሃነትን/ልዩነትን በት/ቤት አቻችሎ ለመቀበል የሃኪም ምርመራ፣ ህክምና፣ እና/ወይም ሌሎች ሠነዶች አስፈላጊ አይሆኑም።
- ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን ያልገለጹ ተማሪዎች ስለ ጾታ ማንነታቸው ለመወያየት እና የጾታ ምንነታቸውን በግልጽ ለማረጋገጥ እና መቼ፣ ከማን ጋር፣ እና ምን ያክል ግላዊ ገበናን መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመለዋወጥ የመወሰን መብት አላቸው። ተማሪዎች ለሠራተኞች ወይም ሌሎች ተማሪዎች ስለጾታ አቋም ለመግለጽ ፈቃደኞች ሆኑ ማለት በህጋዊነት አስፈላጊ ካልሆነ ወይም እንዲገለጽ ተማሪዎቹ ኃላፊነት ሰጥተው ካልሆነ በስተቀር የት/ቤት ሠራተኞች የተማሪዎችን አቋም ለሌሎች ወላጆች/ሞግዚቶች እና ሌሎች የት/ቤት ሥራ ባልደረቦችን ጨምሮ ይፋ እንዲያደርጉ ፈቀዱ ማለት አይደለም። ጾታ የቀየሩትን ወይም ጾታቸውን ያላረጋገጡ ተማሪዎችን በት/ቤት ድጋፍ ለመስጠት አስፈላጊ ከሚሆነው የበለጠ በርካታ ጥያቄዎችን መጠየቅ አግባብ አይደለም።

## ስሞች/ተውላጠ ስሞች

- ሁሉም ተማሪዎች በመረጡት ስም እና/ወይም ተውላጠ ስም የመጠራት መብት አላቸው። የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች ተማሪዎችን መጥራት ያለባቸው በት/ቤት ውስጥ ዘወትር በሚጠሩበትና ከፆታ ማንነታቸው ጋር በሚገጣጠም የተረጋገጠ ስም/ተውላጠስም መሆን አለበት። ተማሪዎች ስለ ስም ስያሜ እና/ወይም ስለ ጾታ ስያሜ ለውጥ ወይም የተማሪ ሪኮርዶችን ማስለወጥ እነርሱ ከመረጡት ስም ጋር የሚጣጣም ስም እና ተውላጠ ስም ለመለወጥ እንደቅድመ ሁኔታ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አይጠበቅባቸውም። በተቻለ መጠን፣ እና ከዚህ መመሪያ ጋር በማጣጣም የት/ቤት ሠራተኞች ፆታ የቀየሩ ተማሪዎችን አቋም/ገመና በሚስጥር ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ አለባቸው።
- ት/ቤቶች በተማሪ ሪኮርድ እና በሌሎች ሠነዶች ላይ የተማሪን ህጋዊ ስም ወይም በተወለዱበት ጊዜ የተሰጣቸውን የጾታ ስያሜ ለመጠቀም በህግ ባልተጠየቁ ጊዜ ሁሉ ለክፍል የተማሪዎች መዝገብ፣ ለመታወቂያ ባጆች፣ ለማስታወቂያዎች፣ ለሠርተፊኬቶች፣ ለጋዜጦች፣ ለመጽሔቶች፣ እና ለዓመታዊ መጽሔት ጭምር ት/ቤቶች በተማሪው(ዋ) የተመረጠውን ስም እና ጾታ መጠቀም አለባቸው።
- በተማሪ ወይም በወላጅ/ሞግዚት ተለይቶ የተገለጸ ካልሆነ በስተቀር፣ የጾታ ለውጥ ያደረገ/ች ተማሪን ወላጅ/ሞግዚት መገናኘት ሲያስፈልግ፣ የ MCPS ት/ቤት ሠራተኞች ተማሪው(ዋ) በተወለደ(ች)በት ወቅት ከተሰጠው/ከተሰጣት ስያሜ ላይ ያለውን ህጋዊ ስም እና የተውላጠ ስም መጠቀም አለባቸው።

## ይፋ የት/ቤት ሪኮርድ

- ት/ቤቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ ህጋዊ ስም እና ፆታ የሚገልጽ ቋሚ የሆነ ፋይል/መዝገብ ሊኖራቸው ይገባል። ደረጃ ለጠበቀ ፈተናዎች/ቴስት ወይም ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ/ዲፓርትመንት (MSDE) የሚቀርቡ ሪፖርቶች ለመሣሠሉት፣ት/ቤቶች ከተማሪ ቋሚ ሪኮርድ ህጋዊ ስም እና ጾታ መጠቀም በሚያስፈልግበት ሁኔታዎች፣ ተማሪው(ዋ) ከመረጠ(ች)ው የሚለይ ከሆነ ህጋዊውን ስም የት/ቤት ሠራተኞች እና አስተዳዳሪዎች ሳይታሰብ ማጋለጥን ማስወገድ አለባቸው።
- ህጋዊ ስም ወይም ጾታ መቀየሩን ዶኩሜንት በሚቀርብበት ወቅት በተማሪ ህጋዊ ስም ወይም ጾታ የተደረገውን ለውጥ ለማንጸባረቅ የተማሪ ቋሚ ሪኮርድ መቀየር/መለወጥ አለበት። ከሚከተሉት ሠነዶች/ዶኩመንቶች የትኛውም የህጋዊ ስም እና/ወይም የጾታ ለውጥ ማስረጃ ነው:-

  - የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣
  - አዲስ የልደት ሠርተፊኬት፣
  - ከ ስቴት- ወይም ከፌደራል- የተሰጠ መታወቂያ፣ ወይም
  - ፈቃድ ካለው/ካላት የጤና ባለሙያ የተሰጠ ማስረጃ።
- ተማሪው/ዋ ወይም የተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ እነዚህ ማስረጃዎች ሳይኖሩ የተማሪው/ዋ ህጋዊ ፋይል እንዲቀየር ከጠየቁ ት/ቤቱ OSFSE ን መጠየቅ አለበት።
- በተማሪ ህጋዊ ስም እና/ወይም ጾታ ለውጥ ከተደረገ በኋላ ት/ቤት የቀድሞውን የተማሪ ማንነት መጠበቅ/መከላከል አለበት። ተጨማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት እባክዎ Student Record Keeper Manual, Office of Shared Accountability (OSA), OSFSE ይጠይቁ።
- በት/ቤት ህጋዊ ሪኮርዶች ላይ የስም ወይም የጾታ ለውጥ ከተደረገ በኋላ፣ ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) እንዲያስውቅ ት/ቤቱ ለ OSA መግለጽ አለበት።
- በይፋዊ የት/ቤት ሪኮርዶች ላይ የስም እና/ወይም የጾታ ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ማናቸውንም በሌላ ምንጭ የተሠሩ ወቅታዊ ሪኮርዶችን (ለምሳሌ፡- የክትባት ሪኮርዶችን፣ የዶክተሮች ሪኮርዶችን፣ ወይም ከሌሎች የህክምና ባለሙያዎች ሪኮርዶችን) ለት/ቤት እንዲያቀርቡ ቤተሰቦችን ማማከር/መንገር አለባቸው።
- በተመሣሣይ፤ የቀድሞ ተማሪ ህጋዊ ስም ወይም ጾታ መለወጡን የሚያረጋግጥ ሠነድ በፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ በአዲስ የልደት ሠርተፊኬት፣ ከስቴት ወይም ከፌደራል የተሰጠ መታወቂያ፣ ወይም ሠርተፊኬት ያለው/ያላት የጤና ባለሙያ በሚቀርብ ዶኩመንት መሠረት የተቀየረውን የቀድሞ ተማሪ ስም እና/ወይም ጾታ እንዲያንጸባርቅ የቀድሞ ተማሪ ነባር ሪኮርድ መቀየር አለበት። እነዚህ ለውጦች የሚከናወኑት በማእከላዊ ሪኮርዶች/መረጃ ነው።

## የአለባበስ ደንብ/ሥርዓት

- ጾታ የቀየሩ ወይም ጾታቸውን የማይገልጹ/የማያረጋግጡ ተማሪዎች የ MCPS የአለባበስ ኮድ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ፣ የጾታ ማንነታቸውን ወይም ጾታቸውን ገላጭ የሆነ አለባበስ የመልበስ መብት አላቸው። የትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች ጾታ በቀየሩ ወይም ጾታቸውን ለይተው ያላሳወቁ/የማያረጋግጡ ተማሪዎች ላይ ስለ አለባበስ ኮድ በሌሎቹ ተማሪዎች ላይ ከሚያደርጉት የተለየ ጫና ማድረግ አይኖርባቸውም።
- ለክፍል ወይም ዓመታዊ መጽሐፍ/መጽሔት ፎቶ፣ የላቀ ትምህርት ለሚማሩ ማህበረሰብ በዓላት፣ ለምረቃ በዓላት፣ ወይም የዳንስ ዝግጅቶች ሲኖሩ ት/ቤቶች ጾታዊ አለባበስን የማይመለከት (gender neutral dress codes) የአለባበስ ሥርዓት መከተል አለባቸው። በተጨማሪም፤ በጾታ የተለየ ልብስ በሚለበሱበት ሁኔታዎች (ለምሳሌ፡- በትእይንቶች እና ትርኢቶች ጊዜያት)፣ ተማሪዎች ከጾታ መገለጫቸው ጋር የሚስማማ ልብስ እንዲለብሱ መፈቀድ አለበት።

## ፆታን-መሠረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች

- ት/ቤቶች በጠቅላላ በጾታ ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ እና አፈጻጸሞችን መገምገም ይኖርባቸዋል፣ እና ከትምህርታዊ ዓላማ ጋር የሚስማሙትን ብቻ መጠበቅ አለባቸው። በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም ሌሎች ህጋዊ በሆነ ጾታ-ተኮር ህግ፣ ፖሊሲ፣ ወይም አፈጻጸሞች፣ ተማሪዎች በጾታ በሚለዩበት ማናቸውም ጊዜ ተማሪዎች ከጾታ ማንነታቸው ጋር የሚጣጣም ተሳትፎ እንዲያደርጉ መፈቀድ አለበት።

## ፆታ-የሚለይባቸው አካባቢዎች

- መገልገያዎች በፆታ ተለይተው ለተማሪዎች ሲመደቡበፆታ ተለይቶ የሚመደብ መገልገያዎችን እንዲጠቀሙ (ለምሳሌ፡- መፀዳጃ ቤቶች፣ እቃ መቆለፊያ ክፍሎች፣ እና ልብስ መቀየሪያ ክፍሎች) ከተረጋገጠው ፆታ መለያቸው ጋር የሚጣጣም በሆነ መልኩ መሰጠት አለበት።
- ለደህንነት ሲባል፣ ግላዊ/ገበና፣ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ማናቸውም ተማሪ የጋራ መገልገያዎችን ለመጠቀም አመቺነት ካልተሰማው/ት፣ ጥያቄ ሲቀርብ፣ ሠላማዊ እና ማሸሚጠጥ የሌለበት አማራጭ፤ ለብቻ የመፀዳጃ ክፍል፣ ወይም የሎከር ክፍሎችን የመሣሠለ፣ ልብስ መቀየሪያ ለብቻ ለመገልገል የሚያስችል መጋረጃ በቅርብ ያለ የግል መጸዳጃ ክፍል ወይም ቢሮ፣ ወይም የተለየ የልብስ መቀየሪያ መርሃግብር መሰጠት አለበት። ተማሪው/ዋ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መደረግ ያለበት ሚስጥራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።
- በፆታ አምሳያነት ካላቸው ተማሪዎች ጋር በጋራ ለመጠቀም ለሚችሉ ተማሪዎች ሌላ አማራጭ እንዲዘጋጅላቸው አያስፈልግም። አማራጭ ሁኔታ ለመጠቀም በተማሪው/ዋ ጥያቄና የጾታ ለውጥ ያደረገ/ች ተማሪን ግላዊ ሚስጥር ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ ነው።
- አንዳንድ ተማሪዎች በፆታ ተለይቶ የተመደበ መገልገያ ፆታው(ዋ)ን ከቀየረ/ች ተማሪ ጋር ለመጠቀም አይመቻቸውም ይሆናል። ይሄ ያለመመቸት ፆታው(ዋ)ን ለቀየረ/ች ተማሪ እንዳይ(ት)ጠቀምበት ለመከልከል ምክንያት ሊሆን አይችልም። ስለ ጾታ ማንነት ግንዛቤ እንዲኖር እና የሁሉንም ተማሪዎች ባህልና ወግ ማክበርን ለማዳበር ተማሪዎች ያልተመቻቸውን ሁኔታ ለማስተካከል የት/ቤት አስተዳዳሪዎች እና ካውንስል የሚያደርጉ የሥራ ባልደረቦች ከተማሪዎች ጋር መሥራት አለባቸው።

## አዲስ ግንባታ/እድሳት፡-

- የት/ቤት አስተዳደር ለተማሪዎች ጾታን የማያገል/gender-neutral መጠቀሚያ ለመስጠት አሁን ያሉት መገልገያዎች መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆነ ት/ቤቶች መጠቀሚያዎችን ለማዘጋጀትና አሁን ያሉትንም ማሻሻል ወይም ማደስ ጭምር የሚያካትቱ እቅዶችን ከመገልገያዎች ማደራጃ/አስተዳደር ዲፓርትመንት ጋር አብረው መሥራት አለባቸው።
- ለተማሪዎች ሠላም/ደህንነት ግንዛቤ በመስጠት፣ የመገልገያዎች አስተዳደር ዲፓርትመንት ጾታ-ገለልተኛ የሆነ መጸዳጃ ለተማሪ/ለህዝብ መጠቀሚያ ንድፍ/ዲዛይን ማዘጋጀት አለበት።
- አስፈላጊነቱ ከታመነበት፣ MCPS በእያንዳንዱ ደረጃ-ፎቅ/ፍሎር እና ሰው በሚበዛበት አካባቢ ቢያንስ አንድ ፆታ-ገለልተኛ ሽንት ቤት መስራት አለበት።
- በተቻለ መጠን፣ MCPS ቢያንስ አንድ ጾታ-ገለልተኝነት ያለው የአልባሳት መቀየሪያ በአዲሶቹ ት/ቤቶች እና የት/ቤት እድሳት ዲዛይኖች ላይ ማካተት ያለበት ሲሆን፣ ጾታ-ገለልተኛ የሆነ መገልገያ ዲዛይን ሲዘጋጅ ለደህንነት የማያሰጋ ሠላማዊ እና ገበናን ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑ በዲዛይኑ እና በቦታ አመራረጡ ግንዛቤ ዉስጥ መግባት አለበት።

## የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት እና በት/ቤቶች ውስጥ የሚካሄድ ስፖርት

- ምንጊዜም ት/ቤት በጾታ-የተለየ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት ሲሰጥ እና በት/ቤቶች ውስጥ ባሉ ስፖርቶች፣ ተማሪዎች ከፆታ መለያቸው ጋር በሚመጥን ስፖርት እንዲሳተፉ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

## በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ

- በትምህርት ቤቶች መካከል በሚካሄዱት አትሌቲክስ ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን በግልጽ የማያሳውቁ ተማሪዎችን ተሳትፎ በ Maryland Public Secondary Schools Athletic Association (MPSSAA) ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ቀጥሎ ባለው ድረ-ገጽ ላይ እንደሚገኘው ይወሰናል https://www.mpssaa.org/assets/1/6/MPSSAA_Transgender_Guidance_revised_8.16.pdf።
- ተመጣጣኝነት ያለው ፍትኃዊነት ለማረጋገጥ ከ MPSSAA መመሪያ አኳያ፣ የሴቶች የተሟላ የስፖርት ተሳትፎ እና ያለ አድሎአዊነት እኩል የመሣተፍ እድሎችን፣ ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን በግልጽ የማያሳውቁ ተማሪዎች በ MCPS በትምህርት ቤቶች መካከል በሚደረጉ የአትሌቲክስ ቡድኖች እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት፡-
  - ተማሪ በተወለደ(ች)በት ወቅት የተሰጠ የጾታ ስያሜ፤ ወይም
  - ተማሪው(ዋ) ያስለወጠ(ች)ው ጾታ፣ ወይም
  - በተማሪው(ዋ) የተረጋገጠ የጾታ ማንነት።
- ማናቸውንም በት/ቤቶች መካከል የሚደረጉ አትሌቲክስ በሚመለከት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ት/ቤቶች ለ MCPS አትሌቲክስ ክፍል ማስተላለፍ አለባቸው።
- በሌሎች ት/ቤቶች የሚደረግ ውድድር፡- በተማሪ ስምምነት እና የተማሪው(ዋ) አገልግሎት አካል ተደርጎ በአካባቢ ት/ቤት የሚሰጠው አይነት መገልገያ በሌሎችም መገልገያዎች/facilities እንዲኖር መደረግ አለበት። ኮች/አሰልጣኝ ወይም ተማሪው/ዋ የሚ(ምት)ማርበት ት/ቤት በሌላኛው በሚጎበኘዉ ት/ቤት ስለ ማንኛዉ ም አስፈላጊ ነገሮች፣ የተማሪው/ዋ ማንነት በሚስጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ማሳወቅ አለበት/አለባት።

## ከክፍል ውጭ ትምህርት/በምሽት የመስክ ጉዞዎች

- ተማሪዎች ባረጋገጡት የፆታ መለያቸው ጋር በሚጣጣም ሁኔታ እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት።
- ስለመኝታ ቦታ/ሁኔታ ዝግጅት ከተማሪው/ዋ እና ከቤተሰብ (ቤተሰብ ተማሪውን/ተማሪዋን የሚደግፍ ከሆነ) ጋር መወያየት ያስፈልጋል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና ጥያቄ ከቀረበ፣ ሠላምና ደህንነት የተጠበቀና ማሸሚጠጥ የሌለበት አማራጭ የግል መኝታ አካባቢ የመሳሰለ መሰናዶ መሰጠት አለበት።
- ት/ቤቶች ማናቸውንም የግል ገበና ለመጠበቅ የሚፈልግ/የምትፈልግ ተማሪ፣ በተቻለ መጠን፣ ከሌሎች ተማሪዎች ባለማግለል ለማስተናገድ መሞከር አለባቸው።
- የተማሪ ጾታ መቀየር ሚስጥራዊ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ስለሆነ የት/ቤት ሠራተኞች የተማሪዎችን ጾታ የመቀየር አቋም ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለወላጆቻቸው/ሞግዚቶች የመስክ ጉዞ ጋር በተገናኘ ምክንያት ያለተማሪው(ዋ) ወይም ወላጅ/ሞግዚት ፈቃድ ይፋ ማድረግ አይኖርባቸውም።

## ወከባ/ማስፈራራት እና ትንኮሳ/ማስጨነቅ

- LGBTQ+ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ወከባ/ማስፈራራት እና ትንኮሳ/ማስጨነቅ ያጋጥማቸዋል፣ እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ ራሳቸውን ለማጥፋት/ለመግደል የማሰብ ሁኔታ LGBTQ+ ካልሆኑ ተማሪዎች ይልቅ በአምስት እጥፍ ራስን የመግደል ሙከራ ይታይባቸዋል።
- ስለ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስጨነቅ የቦርድ ፖሊሲ እና ደንብ/MCPS Board Policy JHF and MCPS Regulation JHF-RA ቀጥሎ ባለው የ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/section.aspx?sectionID=10.
- ወከባ-ማስፈራራት እና ትንኮሳ-ማስጨነቅ የሚያካትተው በተማሪው(ዋ) ላይ ያተኮረ ነባራዊ ወይም በግምታዊ አስተሳሰብ የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ እና ተማሪው(ዋ) በሚቀርበው/በምትቀርበው ጓደኛ ባህርይ፣ የቤተሰብ አባል፣ ወይም ሌላ ሰው ወይም ቡድን በተማሪው(ዋ) ላይ ያነጣጠረ ባህርይን ነው።
- በነባራዊ ሁኔታ ወይም በይሆናል በተማሪ የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ ምክንያት ተማሪ ላይ ያነጣጠረ ማስጨነቅ፣ ወከባ፣ እና ማስፈራራት፣ ልዩነት/አድሎ የማድረግ ቅሬታ ሲቀርብ እንደሌሎቹ አድሎአዊነትን የማስወገድ እርምጃ በአንድ ዓይነት መስተናገድ አለበት። ማስፈራራት/ጉልበትን ተማምኖ ሌሎችን ለመጉዳት መፈለግ እና ጥቃት/በደልን ት/ቤቶች በንቃት መጠበቅና ሳይቆይ ወዲያውኑ መፍትሔ መስጠት አለባቸው።
- ጾታቸውን ስለቀየሩ ተማሪዎች እና ጾታ አስረግጠው ስለማይናገሩ ተማሪዎች በት/ቤታቸው ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ እና ተማሪዎች ጾታቸውን የመግለጽ ድፍረት እንዲያገኙ የት/ቤት ሠራተኞች ተገቢ/ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።
- እርግጠኛ በሆነ ወይም በሚጠረጠር የጾታ ማንነት ወይም አገላለጽ ምክንያት ተማሪዎች መቀጣት አይኖርባቸውም።
- በት/ቤቶች በሁሉም LGBTQ+ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ/ማዋከብ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ለመከላከል ፕሮግራሞችን እያዳበሩ የሚመሩ እድሜን - የሚመጥን የተማሪ ድርጅቶች እንዲኖሩ ይበረታታሉ።

## ሰላማዊ ስፍራ

- መተላለፊያ/ኮሪዶር ወይም "ውልብ" ብሎ የሚታለፍበት አስፈላጊ ከሆነ፣ ጾታ የቀየረ(ች) ወይም ጾታው(ዋ)ን በመለየት የማይገልጽ/የማትገልጽ ተማሪ ደህንነት ከማይሰማው/ከማይሰማት ወይም ምቾት ካልተሰማው(ት) በማናቸውም ጊዜ ወደ ሠላማዊ ሥፍራ (ለምሳሌ፡- ዋና ቢሮ፣ ካውንስለር ቢሮ) እንዲሄዱ/እንዲጠቀሙ ት/ቤቶች መፍቀድ ይኖርባቸዋል።
- ሰላማዊ ክልል፡- ት/ቤቶች ከመምህራን ማስተማሪያ ክፍሎች የተወሰኑትን፣ የተወሰኑ ቢሮዎችን፣ ወይም በት/ቤት ውስጥ የተወሰነ ስፍራ ሰላማዊ አካባቢ የሆነ ቦታ፣ ማንኛውም ተማሪ፣በማናቸውም ምክንያት ከትችትና ማንጓጠጥ ነፃ ሆነው መቆየት የሚችሉበት ስፍራ ለይተው መመደብ አለባቸው። በመዝጊያዎቻቸው ላይ "safe zone stickers" ያሏቸው የት/ቤት ሠራተኞች ሁሉን ያካተተ፣ የሚያረጋግጥ አካባቢ አግባብነት ያለው ስልጠና ማግኘታቸውን ት/ቤቶች ማረጋገጥ አለባቸው።

## መገናኛዎች

- የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡- MCPS OSFSE በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4824, ወይም MCPS Office of School Administration, Compliance Unit, በቁጥር፡- 240-740-3215 ያነጋግሩ።

1311.18ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 10/18 • Web